## አዋጅ ቁጥር 171/2012 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የየርከኑን ምክር ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ምርጫ የህዝቡ የስልጣን ባለቤትነት መገለጫ በመሆኑ ህዝቡ የመምረጥ መብቱን በሰፊ ተሳትፎ እንዲያረጋግጥ ለዚሁ የሚረዳ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የምርጫው ሂደት በክልላችን የተጀመረውን የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በሚያጎለብት አግባብ ይካሄድ ዘንድ ተገቢውን የቅድመ ዝግጅት ስራውን በጥራት ማከናወን በማስፈለጉ፤

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ጋር ለማጣጣም የወጣና የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 7 (4)፣8 (2) እና 13(2) ለክልልና ከዚህ በታች ላሉ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ በአንድ ምርጫ ክልል ወይም አካባቢ ምን ያህል ተወካዮች እንደሚመረጡ በየክልሉ ህግ መሰረት መወሰን እንዳለበትና ምክር ቤቶቹ የአባሎቻቸውን ቁጥር (የተወካዮች ብዛት) ለመቀየር ሲወስኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች በቂ የዝግጅት ጊዜ መስጠቱን ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የየእርከኑ ምክር ቤት ተወካዮች ብዛት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር--------/2012 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. **"ክልል"** ማለት የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማለት ነዉ፤
2. "የምርጫ ክልል" ማለት በምርጫ ህግ ወይም በብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ደንብና መመሪያ መሰረት ለምርጫ አፈፃፀም ተግባር በየደረጃ ለሚገኙ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ የተከለለና በየምክር ቤቶች የተወሰነ ብዛት ያላቸዉ ተመራጮች የሚወከሉበት አካባቢ ማለት ነዉ፤
3. "የአካባቢ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው የብሄራዊ ምርጫ ህግ መሰረት የሚካሄድ የብሄረሰብ፣ የወረዳ፣የልዩ ወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ማለት ነው፡፡

4. “ተወካይ” ማለት በብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ጽህፈት ቤት አስፈፃሚነት በሚካሄደዉ የምርጫ ስርዓት አንድን የምርጫ ክልል ወይም አካባቢ በመወከል የሚመረጥ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት፣የብሄረሰብ ምክር ቤት፣ የወረዳና ልዩ ወረዳ ምክር ቤት፣ የከተማ አስተዳደር ምክር ቤትና የቀበሌ ምክር ቤት ተመራጭ ማለት ነዉ፤
5. “የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት” ማለት በክልሉ ውስጥ በየደረጃዉ ባሉ ከተሞች የከተማ አስተዳደር ተቋቋሞላቸው በከተማ አስተዳደሩ ተመራጮች የሚወከሉበት ማለት ነዉ።
6. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ቁጥርን ለመወሰን ሲባል ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ማለት ከ60,000 እና ከዚያ በላይ፣ መካከለኛ የህዝብ ቁጥር ከ25,000 እስከ 59,999፣ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ከ17,000 እስከ 24,999 ህዝብ ማለት ነው።
7. የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ቁጥርን ለመወሰን ሲባል ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ማለት ከ52,000 እና ከዚያ በላይ፣ መካከለኛ የህዝብ ቁጥር ከ25,000 እስከ 51,999፣ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ከ15,400 እስከ 24,999 ህዝብ ማለት ነው።
8. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ቁጥርን ለመወሰን ሲባል ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ማለት ከ5,000 እና ከዚያ በላይ፣ መካከለኛ የህዝብ ቁጥር ከ3,000 እስከ 4,999፣ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ከ2,999 በታች ማለት ነው።

## <u>አንቀፅ 3</u>

## የጾታአገላለጽ

በዚህ አዋጅ ዉስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸዉ የሴት ፆታንም ይጨምራል።

## አንቀፅ 4

## <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ **ክልላዊ መንግስት በየእርከኑ ባሉ ምክር ቤት ተወካዮች** ወይም ተመራጮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ተወካዮች ብዛት

## አንቀጽ 5

## የክልል፣የወረዳ፣የከተማ አስተዳደርና የቀበሌ ምክር ቤቶች ብዛት

ለክልልና ከዚህ በታች ላሉ ምክር ቤቶች አባላት መርጫ በአንድ የምርጫ ክልል ወይም አካባቢ የሚኖሩት ተወካዮች ብዛት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. ለክልል ምክር ቤት በአንድ የምርጫ ክልል ከ4-6 የሚደርሱ ተወካዮች ሆኖ ብዛታቸው ከአንድ መቶ መብለጥ የለበትም፤
2. **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለክልል ምክር ቤት በአንድ የምርጫ ክልል እንደ አስፈላጊነቱ ከ3-7 የሚደርሱ ተወካዮች መምረጥ የሚቻልበት ሆኖ ብዛታቸው ከአንድ መቶ መብለጥ የለበትም፤**
3. ለወረዳ ምክር ቤት የህዝቡን ብዛት መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ወረዳዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ1,000 እስከ 1,700 ህዝብ፣መካከለኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ወረዳዎች አንድ ወኪል በአማካኝ 400 እስከ 999 እንዲሁም ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ወረዳዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ280 እስከ 399 ህዝብ እንዲወከል ሆኖ ከ60-200 ተወካዮች፤
4. ለከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የህዝቡን ብዛት መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ከተማ አስተዳደሮች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ865 እስከ 1,000 ህዝብ፣መካከለኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ከተማ አስተዳደሮች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ400 እስከ 864 እንዲሁም ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ከተማ አስተዳደሮች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ250 እስከ 399 ህዝብ እንዲወክል ሆኖ ከ60-200 ተወካዮች፤
5. ለቀበሌ ምክር ቤት የህዝቡን ብዛት መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ቀበሌዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከአንድ መቶ እና ከዚያ በላይ ህዝብ፣መካከለኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ቀበሌዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ60 እስከ 99 እንዲሁም ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ባላቸው ቀበሌዎች አንድ ወኪል በአማካኝ ከ6 እስከ 59 ሰዎች እንዲወክል ሆኖ ከ50-300 ተወካዮች፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚወከለው የህዝብ ብዛት በአማካኝ ዝቅተኛ በሚል ከተቀመጠው መነሻ የህዝብ ቁጥር በታች ከሆነ ተጨማሪ አንድ ወኪል የሚመርጡ ይሆናል።

## አንቀጽ 6

## ስለ ብሔረሰብ ምክር ቤቶች

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የብሔረሰብ አስተዳደሮች በሚመለከት ያላቸውን የህዝብ ብዛት መሰረት በማድረግ የብሔረሰብ ምክር ቤቶች አባላት ቁጥር በሚከተለው አኳኋን ተወስኗል፡-
   ሀ) 200,000 እና ከዚያ በታች ቕሰህዝብ ቁጥር ባላቸው የብሔረሰብ አስተዳደሮች ለክልል ምክር ቤት አባልነት የሚመረጡትን ጨምሮ ከ30 እስከ 70 የብሔረሰብ ምክር ቤት አባላት ይኖራሉ፤
   ለ) ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ከፍ ያለ የህዝብ ቁጥር ባላቸው የብሔረሰብ አስተዳደሮች ለክልል ምክር ቤት አባልነት የሚመረጡትን ጨምሮ ከ71 እስከ 100 የብሔረሰብ ምክር ቤት አባላት ይኖራሉ፡፡
2. በክልል ምክር ቤት አባልነት ከተመረጡት ውጭ ያሉት የብሔረሰብ ምክር ቤት አባላት በብሔረሰብ አስተዳደሩ ስር ካሉት ከእያንዳንዱ የወረዳና የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች የየምክር ቤቶቹን አባላት ቁጥር ግምት ውስጥ በሚያስገባ ሁኔታ በእያንዳንዱ ብሔረሰብ ምክር ቤቶች አማካኝነት ይመረጣሉ፤ የአመራረጣቸው ዝርዝር ስነ-ስርዓት በየብሔረሰቡ ምክር ቤቶች የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 7

## ስለ ተወካዮች ብዛት ለውጥ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ስር የተደነገገው ቢኖርም የብሔረሰብ ምክር ቤቶችን ሳይጨምር የክልሉ ምክር ቤት በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ ተወካዮች ብዛት ላይ ማስተካከያ ማድረጉን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የዕጩዎች ምዝገባ ከመካሄዱ በፊት **በምርጫ ህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊለውጠው ይችላል፤**
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተደረገውን የተወካዮች ብዛት ለውጥ ለብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 8

## ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች ህጎችና ማናቸውም ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀጽ 9

## አዋጁን ስለማሻሻል

አዋጁ እንደ አስፈላጊነቱ በክልል ምክር ቤት ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 10

## ???? ? ? ?? ?? ? ? ? ? ???

??? አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችንና መመሪያዎችን የክልሉ ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 11

## አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት---------2012 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሶሳ**

**ጥር---------/2012 ዓ.ም**

**አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ**
**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**
**ፕሬዝዳንት**